ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር
KINIJIT NORTH AMERICA ASSOCIATION OF SUPPORT ORGANIZATIONS (KNAASO)
766 Rock Creek Church Rd. NW. Washington DC. 20010
Tel: (202) 541 0556 Fax: (202) 541-0557 Email: kinijitna@kinijitna.org

ማርች 4 ቀን 2008 ዓ/ም

# ኢሕአዴግ አካሂዳለሁ የሚለው ምርጫ የቀድሞዋን አልባንያ ያስታውሰናል።

ሀገራችንን ኢትዮጵያን ሳናስብ፤ ስለ ወገናችን ደህንነት ሳንጨነቅ፤ ስለናት አባቶቻችን ስለወንድም እህቶቻችን ችግር ሳናሰላስል የማንውልበት ቀን የለም። የሁሉም አገር ዜጋ ስለሀገሩ ማሰቡ ባይቀርም የኛን ከሌላው ለየት የሚያደርጉት ምክንያቶች አሉ። የመጨረሻዎቹ ደሆች ተብለን መፈረጃችን ያንገበግበናል፤ አሁንም የምጽዋዕት ሰንዴ እየጠበቅን መኖራችን ያሳፍረናል፤ ነገ ሊፈነዳ በሚችል የጎሳ ግንኙነት እሳተ ገሞራ ላይ መቀመጣችን እንቅልፍ ይነሳናል፤ ሕዝባችን በወታደር መዳፍ ስር ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቱ ተገፎ መኖሩ ያስቆጣናል፤ የሕዝብ ቁጥር በሚያስደነግጥ ሁኔታ እየጨመረ ኤኮኖሚውና የተፈጥሮ ሃብታችን እየመነመነ መሄዱ ይረብሸናል፤ በአራቱም የዓለም ማዕዘን ስደተኛ ሕዝብ ተብለን መታወቃችን ውስጣችንን ያቆስለዋል። ከላይ የዘረዘርናቸው አንዳችም ቃለ አጋኖ የሌለባቸው ያገራችንና የኢትዮጵያዊነት የወቅቱ ገጽታዎች ናቸው።

የደርግ መንግሥት ለሰፊው ሕዝብ የቆምኩ ነኝ ብሎ ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ የመናገርና የመጻፍ ነጻነቱን ገፈፈ፤ ኢሕአዴግም እንደዚሁ። መሬትን የሕዝብ አደርጋለሁ ካለ በኋላ ካድሬዎቹን ባላባት ገበሬውን ጭሰኛ አደረገ፤ ኢሕአዴግም እንደዚሁ። ኢንዱስትሪና ንግድ ከካፒታሊስቶች እጅ ወጥተው የሕዝብ መገልገያ ይሆናሉ ብሎ ከተገዘተ በኋላ የመንግሥት መገልገያ አደረጋቸው፤ ኢሕአዴግ ደግሞ ይባስ ብሎ ከሕዝብ ነጠቀና በጣት የሚቆጠሩ ወገኖቹን በአንድ ጀንበር ሚሊዮነሮች አደረገባቸው። ሕዝቡ ግን የሚላስ የሚቀመስ እያጣና ቤተሰብ በፈረቃ ከሚበላበትና በፈረቃ ከሚተኛበት አስከፊ የኑሮ ዘመን ላይ ደርሷል። የመንግሥት ፕሮፓጋንዳ "የሚቀደው" እና በአዲስ አበባና በአንዳንድ ከተሞች የሚታየው ብልጭልጭ ለሕዝብ ምኑም አይደለም። የነፍስ ወከፍ የካሎሪ ፍጆታውንም ሆነ የጤንነት ፋይዳውን ፈቀቅ እንኳ አላደረገለትም። ፍጥጥ ያለው የሀገራችን እውነታ ይህ ሆኖ እያለ ሌላ ሊሰብኩን የሚሞክሩ መኖራቸው ያስገርመናል።

ሀቅን ሊያስተናግድ የሚችል ጠንካራ ሀሊና ላለው በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም፤ ዲሞክራሲና ልማት በዘላቂነት መቀጠላቸውን የሚያረጋግጥ የመንግሥትና የፖለቲካ ስሪት የለም። በኢሕአዴግ ትርጉም ሠላም ማለት "ተቀናቃኞችን አጥፍቶ የሚጣሉት የሌለበት" የፖለቲካ አየር ስለሆነ የለየለት አምባገነንነት ነው። ላንዳንዶች ሠላም "በዝምታና በፍርሀት መገዛት" ነው። ለሌሎች ደግሞ ሠላም "የመደራደርና የመቻቻል" ውጤት ነው። ይኸኛው የሠላም ጎዳና ብቻ ነው ቀጣይ የሆነ መረጋጋትንና የአመጽና የሽብር አለመኖርን የሚያረጋግጥልን።

ውነተኛ መረጋጋት በሌለበት፤ ለአመጽና ለሽብር የሚያመቹ ቀዳዳዎች ባልተደፈኑበት ሁኔታ መብት ዴሞክራሲና ሥልጣን የሕዝብ ይሆናሉ ማለት ዘበት ይሆናል። ስለዚህም ነው ሠላማዊ ትግል በሚያካሂደውና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ደጋፊዎች ባሉት በቅንጅት ላይ በሩን ከዘጋ በኋላ መንግሥት አካሂዳለሁ የሚለው ምርጫ ከመሳቂያና ከመሳለቂያነት የማያልፈው።

"መንግሥት በሩን አልዘጋም፤ ቅንጅት አየለ ጫሚሶ ነው፤ የትኛው ቅንጅት?" የሚለውን ዓይን ያወጣ የኢሕአዴግንና የካድሬዎቹን አሰልች ተረባ ችል ማለት ነው። ሀቁ አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ይካሄዳል የሚባለው ምርጫ በኮሚኒስት ሀገሮች ይካሄድ ከነበረው የውሸት ምርጫ በይዘትም በቅርጽም አንድ መሆኑ ነው። ሕዝብን በግዴታ ማስመዝገብ፤ ኢሕአዴግን ካልመረጥህ ማሳህ ይነጠቃል፤ ከሥራ ትባረራለህ፤ ዕድገትህ ይገታል እያሉ ቅጥ ያጣ ወከባ መካሄድ የዛሬ 18 ዓመት ወደከርሰ መቃብሩ የተሰናበተውን የአልባኒያን ኮሚኒስት ፓርቲ ባህርይ ያስታውሰናል። "ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም" የሚባለው ውነት መሆኑ ይሆን?